EthioLion.Com

# ኢሕአፓ ልዩ ጥሪ ከተደረገላቸዉ ኢትዮጵያዊያን ጋር በለንደን ከተማ የተሳካ ዉይይት አካሄደ

የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አባላት መስከረም 4 ቀን 2001 ዓ.ም. በለንደን ከተማ ልዩ ጥሪ ከተደረገላቸዉ ኢትዮጵያዊያን ጋር የተሳካ ዉይት አካሄዱ። ዉይይት ላይ የተገኙት የከፍተኛ አመራር አባላት አቶ ኢያሱ ዓለማሁና ዶክተር ዘነበ ተሾመ ነበሩ። የድርጅቱ ነባር አባል እና አሁንም ንቁ ተሳታፊ የሆኑት ወይዘሮ ገነት ግርማም በኢትዮጵያ የሕዝባዊ ትግል ታሪክ የሴቶችን ተሳትፎ በተመለከተ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ዉይይቱ የተጀመረዉ ከ1966 ዓ.ም. ጀምሮ እስካሁን ድረስ በሀገራችን በተካሄደዉ ሕዝባዊ ትግል ሻማ በመሆን የወደቁና መከራ የተቀበሉ ሰማእታትን ለመዘከር «ዝክረ-ሰማእታት» በሚል ርዕስ የተዘጋጀ አጭር የምስልና የድምፅ ቅንብር በማቅረብ እና የህሊና ጸሎት በማድረግ ነበር። በማስከተለም ወይዘሮ ገነት ግርማ፡

- ቀደምቱን የሀገራችንን ታሪክ ስንመረምር ሴቶች ከእናትነት የማህበረሰብ ዋልታነታቸዉ በተጨማሪ በአርበኝነትም ሆነ በአስተዳደር መስክ ያደረጉት አስተዋፅዖዋቸው በታሪካችን ተመዝግቦ እንደሚገኝ፤

- በዘመናዊቷ ኢትዮጵያም በለውጥ ፈላጊው የተማሪዎች እንቅስቃሴም ሆነ የፖሊቲካ ድርጅቶች በተለይም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ባካሄደው ሕዝባዊ ትግል የኢትዮጵያ ሰቶች ተሳትፎ ከፍተኛ ቦታ እንዳለው፤
- ፓርቲውም ለሕዝባዊ ትግሉ መሳካት ሴቶችን ጨምሮ የማህበረሰቡ የተለያዩ ክፍሎችን ሙሉ ተሳትፎ አስፈላጊነት በመገንዘብ ካደረገው ጥረት በተጨማሪ አሁንም ላሉት የተለያዩ የፖለቲካ እንቅስቃሴ አራማጆች ትምህርት እንደሆናቸው፤

- አሁንም የምንመኘው ሕዝባዊ የአንድነትና የዴሞክራሲ ትግል ግቡን ሊመታ የሚችለው በሴቶች ሙሉ ተሳትፎ መሆኑን በማስገንዘብ ማብራሪያቸዉን አጠቃለዋል።

በመቀጠልም ገለፃ ያደረጉት ዶክተር ዘነበ ተሾመ የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አባል ነበሩ። እሳቸውም ሕዝባዊ መብት ለማስከበር ቆሚያለሁ ያለ ሁሉን ከማመን በፊት ቃልና ተግባርን መመርመር እንደሚያሻ አስገንዝበዋል። የአንድ ድርጅት ፖሊሲ ሕዝባዊነት የሚለካውም የግለሰብን ሰብአዊ መብትና ተሳትፎ ከማክበር ጋር የሀገርን ሀብት ስርጭት፤ ሉዐላዊነት፤ የሕዝቡን ማህበራዊ፤ ባህላዊ እና ሌሎችም መብቶች ምን ያህል ጠብቀዋል? ወዘተ ለሚሉት መሰረታዊ ጥያቄዎች በሚሰጠው መሪ መልሶች መሆን አለበት ብለዋል። በተጨማሪም፡

- ኢህአፓም በሀገራችን ከነበሩና ከአሉ ፖለቲካዊ፤ ማህበራዊ እና ምጣኔ ሃብታዊ ችግሮች መንጭተው ያነሳቸዉ የህዝብ ስልጣን ባለቤትነት፤ የተለያዩ የማህበረሰባችን ክፍሎች የእኩልነት፤ የሕዝብ የመሬት ባለቤትነት፤ የተመጣጠነና የፍታሐዊ ምጣኔ ሀብት ክፍፍል፤ በነፃ የመደራጀት፤ በነፃ የመንቀሳቀስ፤ በነፃ ሃሳብን የመግለጽ፤ በፖለቲካው ሂደት በነፃ የመሳተፍ እና የመሳሰሉት ሕዝባዊ ጥያቄዎች አሁንም ድረስ እንዳልተመለሱ፤

- ለእነኝህ ጥያቄዎች መልስ ለማስገኘት ኢሕአፓ በአለፉት 36 ዓመታት ባካሄደው ትግል በማንኛውም መንገድ ድርጅትን ለስልጣን በማብቃት ፈንታ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱና የሀገሩ ሉዓላዊነት ተጠብቆ የስልጣን ባለቤትነቱ እንዲረጋገጥ ቃል ኪዳኑን ጠብቆ በመቆሙና በመታገሉ፤

- የአምባገነኖች፤ የጠባቦችና የፀረ-ኢትዮጵያ ሃይሎች ዒላማ ሆኖ ከፍተኛ መስዋዕትነት በፅናት እንደከፈለና በመክፈልም ላይ እንደሚገኝ፤

- ምንም እንኳ ይህ ትግል ገና ለተሟላ ድል ባይበቃም ኢሕአፓ በግንባር ቀደም የፖለቲካ ድርጅትነት ፈር በመቅደዱ:

- ቀደም ሲል የተነሱት ሕዝባዊ ጥያቄዎች የትግሉ መርሆዎች መሆናቸው፤ ጥያቄዎቹም እንዲመለሱ ሕዝቡ ተደራጅቶ መታገል እንደሚያሻው ግንዛቤ ማግኘቱ፤ ለመብትና ለእኩልነት አምባገነኖችን መታገል እንደሚያስፈልግና ይህንንም ለማድረግ እንደሚቻል በአባላቱ ፅናትና መስዋዕትነት በተግባር ማሳየቱ በአምንታዊነት ሊጠቀሱ የሚችሉ መሆናቸውን ገልፀዋል::

አቶ ኢያሱ ዓለማየሁ ደግሞ የሀገራችንና የአንድነት ሃይሉን ወቅታዊ ሁኔታ አስመልክቶ በሰጡት ማብራሪያ:

- የወያኔ አገዛዝ ለውጭ ምሥል ማሳያነት (ለጭምብልነት) ይጠቀምባቸው የነበሩትን አንዳንድ የህጋዊ የማስመሰያ እንቅስቃሴዎች መግታቱን፤

- እምነቱን በደህንነትና በወታደራዊ ጡንቻው፤ በባዕዳን የጡት አባቶቹ እርዳታ ላይ አድርጎ፣ ከጥቂት የአንድ ክልል ሰዎች ስብስብነትም ብሶ የአንድ መንደርና ያምቻ ጋብቻ ገዢዎች አገዛዝ ቡድንነት ጠቦ መጠናከሩን፤

- አገዛዙ በሚያራምደው ፀረ-ህዝብና ከፋፍለህ ግዛው ፖሊሲ ሰበብ በየአካባቢው ለሚከሰቱ ሕዝባዊ እምቢታዎች ወያኔ በሚወስደው ዘግናኝ እርምጃ ለወደፊቱ ችግር እየተደገሰልን መሆኑን፤

- ለሀገራችን ቀና አመለካከት የሌላቸው የውጭ ክፍሎች ከራሳቸው ጥቅም አንፃር ከአንድነት ኃይሉ ይልቅ ጠባብ ሃይሎችን በማጠናከሩ ላይ ማተኮራቸውን፤

- የአንድነት ኃይሉ በራሱ ውስጣዊ የአመራር ችግርና በሰርጎ ገብ ከፋፋዮች በመታመሱ መዳከሙን፤

- በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያና የህዝቡዋ ህልውና አደጋ ላይ መሆናቸዉን ገልፀዋል:: የወያኔ አገዛዝ ስልጣኑን በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ለሕዝብ እንደማያስረክብ ካለፉት 17 ዓመታት ተመክሮ ትምህርት ወስደን የአንድነት ኃይሉ ሁለገብ ትግሉን ማፋፋም እንደሚያስፈልግም አስገንዝበዋል::

EthioLion.Com

በመጨረሻም ከታዳሚዎቹ የተለያዩ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ተሰጥተው ገንቢ ውይይት ተካሂዷል፡፡ የሀገር አንድነትና የሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብት ጥያቄ አንስቶ የታገለው ያ ትውልድ የመሰረተው የኢ.ሕአፓ አባላት እምነት፤ ፅናትና ቆራጥነትም ብዛት ባላቸው ታዳሚዎች ተዘክረዋል፡፡ የወደቁት ጓዶቻቸው የትግል ሻማ እንዳይጠፋም ለትግሎ ነው ሕይወቴ ብለው ሸብረክ ሳይሉ ትግሉን ለቀጠሉት የኢ.ሕአፓ አባላትም ያላቸውን አክብሮትና አድናቆት ብዙ ተናጋሪዎች ገልፀዋል፡፡ የድርጅቱን ነባር የአባላት ፅናትና ቆራጥነት፤ እምቢ ባይነትና ሀገር ወዳድነት አሁን ባለው ወጣት ትውልድ ውስጥ በማስረፅና በማሰባሰብ፤ ሕዝባዊነታቸዉ ጥያቄ ላይ የማይወድቅ ቀደምት አባላትንም ለማሳተፍ በመጣር በወያኔ አገዛዝ ላይ የሚካሄደውን ትግል በመምራት ኢ.ሕአፓ ከሰማዕታቱ የተቀበለውን አደራ ይወጣ ዘንድ ታዳሚዎች በተደጋጋሚ ጥሪያቸዉንና ድጋፋቸዉን አቅርበዋል፡፡

በዝግጅቱ ላይ የድርጅቱን ታሪክ የሚዘክሩ፤ አሁን ያለውን ሁኔታና መጭውን ትግል የሚያመላክቱ ፅሁፎች፤ የድምፅና የምስል ቅንብር ሲዲዎች፤ «የደርግ የአስራት ዘመን» በሚል በቅርቡ የታተመው አዲስ መፅሐፍ፤ ፖስት ካርድና የቀን መቁጠሪያ በነፃና በክፍያ ለታዳሚዎቹ ቀርበው ነበር፡፡

EthioLion.Com